የኢትዮጵያ
ዴሞክራሲያዊ
አንድነት ንቅናቄ

# የነገ ተስፋ

ቅፅ ፩ ቁጥር ፩
የካቲት ፴ ቀን
፪ ሺህ ፪ ዓ/ም

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ ልሳን
ኢዴአን ፖ.ሣ.ቁ.(P.O.Box) 55932* አ.አ.፤ ኢትዮጵያ (A. Abeba, Ethiopia);Email:edum2002@yahoo.com

*እኛ የነገ ታሪካዊ ኃላፊነት ያለን የዛሬ የአገሪቱ ዜጎች ነን:: ከትላንት ቀደሞቻችን የተረከብነውን ጥሩ ጎኑን አዳብረን፣ የጎደለውን አሟልተንና የጎደፈውን ጥለን፣ የእኛን ኀልውና ዛሬ አስቀምጠን እናልፋለን:: አገራችን ነበረች:: አገራችን አለች:: አገራችን ትኖራለች:: ከዚኽ እይታ አኳያ ነው የእኛ የፖለቲካ ተስፋችን ትርጉም ያለው:: ነገ፣ የዛሬዎቹ ዜጎች፣ ለነገዎቹ ተጠያቂዎች ነን:: ተስፋቸውም ነን::*

## <u>ርዕሰ-አንቀፅ፤</u>

### <u>የጋራ ትግል መተባበርን ብቻ ሣይሆን መከባበርን ይጠይቃል፤</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴአን) ውድ አገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆ፣ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነው ሕዝቧ እኩልነትንና ፍትኅን፣ የሕግ-የበላይነትንና ሰላምን የሚያሰፍን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንዲጎናፀፍ ለማስቻል በሚከተለው የሰላማዊ ትግል መርኅ መሠረት፤ በአገሪቱ ያለው የፖለቲካ ምኅዳር በሚፈቅደውና ሁኔታው ማሠራት በሚችለው መጠን የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል:: ኢዴአን የደርግን አስከፊ አገዛዝ ገና ከጅምሩ ከታገሉት ቀደምት ድርጅቶች አንዱ የሆነውና ብቸኛው ተራማጅና እንበለ-አክርሮ (የሊበራል) ዴሞክራሲ እምነት ተከታዩን የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትን (ኢዴኅ) አርማ አንግበው እንዲሁም በልዩ ልዩ ድርጅቶችና በተናጠል ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለፍትኅና ለእኩልነት የታገሉ አባላትን አሰባስቦና አቅፎ በአዲስ መንፈስ፣ አደረጃጀትና አወቃቀር በአዲስ መንፈስ፣ አደረጃጀትና አወቃቀር የተቋቋመ አገር-አቀፍ ድርጅት ነው::

ሰላምን፣ ፍትኅን፣ እኩልነትንና አንድነትን ለማረጋገጥ የሚደረገው ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ትግል በብሔራዊ መግባባት ላይ ሊመሠረትና እነዚኽም እውን መሆን የሚችሉት በተባበረና በተቀነባበረ ሰላማዊ ትግል እንደሆነ ድርጅታችን በመርኅ ደረጃ የተቀበለው ብቻ ሣይሆን በተግባር እያዋለው ያለና ወደፊትም የሚታገልበት የአሠራርና የአካሄድ  መተክሉ ነው:: ከዚኽ መረታዊ እምነቱ በመነሣትም ነው ስምንት ኅብረ-ብሔራዊና የአካባቢ ድርጅቶች ስብስብ የሆነው "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)" እንዲመሠረት ከጅምሩ አንስቶ ተሣታፊ የሆነውና መድረኩ በተመሠረተበት መንፈስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል  አቅሙ በፈቀደ መጠን አስተዋፅዖ እያደረገ የሚገኘው::

በተለይ እንደ አገራችን ስብጥርጥሩ በወጣና ቁጥሩ እጅግ በበዛ መልክ ድርጅት በተትረፈረፈበት አገር ለሥርዓት ለውጥ የሚደረግ ትግል ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ ከትብብር ውጭ ሌላ መንገድ የለም:: መድረክ በተለያየ መልክ ተደራጅተው ለአገራችንና ለሕዝቧ በጎና አወንታዊ ለውጥን ለማስገኘት የሚታገሉ ድርጅቶች በተናጠል የቆሙበት ትግል የተሻለ ግቡን የሚመታው ከመሰል ድርጅቶች ጋር ትግላቸውን ሲያስተባብሩ እንደሆነ በመገንዘብ ያቋቋሙት የትግል መሣሪያ ነው:: ትግሉ ለአገርና ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ ደግሞ አባል ድርጅቶች ትኩረት ሊሰጡት የሚገባው ጉዳይ ዋነኛ በሆኑ የትብብሩ የጋራ ዓላማዎች ዙሪያ ሊሆን እንደሚገባ ግልፅ ነው:: የጋራ ትግሉ ለውጤት እንዲበቃም በልዩነት ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ መሥራት የመጀመሪያውና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ግንዛቤ ስለሆነ አባል ድርጅቶች ንጥጥራቸው በሚያለያዩአቸው በርካታ ነጥቦች ዙሪያ ሣይሆን በቁጥር ጥቂት ሊሆኑ ቢችሉም በሚያግባቧቸው አገራዊና ሕዝባዊ በሆኑ ዓብይ ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል:: የጋራ ትግል በተለ-

*ይም ለዴሞክራሲ የሚደረግ ትግል የሚጠይቀውም ይኸንን ነው:: በልዩነት አብሮ መሥራት ደግሞ ቀናነትንና መቻቻልን ብቻ ሣይሆን መከባበርን በእጅጉ ይጠይቃል። ይኸ ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው ሰላማዊ መንገድ ሊመጣ ቀጭን ዕድል ለሚኖረው መንግሥታዊ ለውጥ ብቻ ሣይሆን ይበልጡን በአገራችን በሕዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተና ሕዝብ ይሁንታውን የሰጠው ፍትኃዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና ዴሞክራሲ ሥር እንዲሰድ አስፈላጊ ለሆነው አገራዊ እርቅና ሰላም ሂደት አስፈላጊ መሠረትና መንደርደሪያ እንደሚሆን እምነታችን ነው::*

*ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሚደረገው ሰላማዊ የኅብረት ትግል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለን አባል የሆንበትና የጋራ መታገያ ቤታችን የሆነው መድረክ ውስጥ በዋናነት ድርጅታችንን ጨምሮ በአንዳንድ አባል ድርጅቶች ዘንድ ቅሬታን የፈጠረ የአሠራር እክል መከሰቱ ይታወቃል:: ኢዴአንም እንደማንኛውም ኃላፊነት የሚሰማው ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ጉዳዩ በመድረኩ መተዳደሪያ ደንብና የጋራ የስምምነት ሰነድ መሠረት መፍትሔ እንዲሰጠው በቀና መንፈስ አበክሮ አሳስቧል፣ ጥረትም አድርጓል::*

*በቅርቡ ይኸንን ችግር ተከትሎና በሱም ምክንያት የድርጅታችን ሊቀ-መንበር በሁኔታው በማዘን ለጊዜው ከመድረኩ ስብሰባ አቋርጠው መውጣታቸውና ይኸም እርምጃ ድርጅታችን ከመድረክ እንደወጣ ተደርጎ በተሳሳተ መልክ መተርጎሙ ይታወቃል:: ይኸ ሁኔታ እንዴትና ለምን እንደተፈጠረ ድርጅቱ በሚከተለው ዴሞክራሲያዊ አሠራር ተወያይቶበታል:: ድርጅታችን ከሌሎች የትግል አጋሮቹ ጋር በማበር ካቋቋመው መድረክ እንዳልወጣና ይበልጥም የሚከሰቱ ስህተቶች በአግቦና በሥርዓት በወቅቱ እየተፈቱ የተያያዝነው ሰላማዊ የጋራ ትግል ለውጤት እንዲበቃ የሚጠበቅብንን ከማድረግና አስተዋፅዖአችን ጎልብቶ እንዲቀጥል ያለንን ቁርጠኝነት ስንገልፅ፣ በአኳያው በመድረኩ ውስጥ ባሉ የተወሰኑ ወገኖች በምርጫው የአባላት አመዘጋገብን በተመለከተ በድርጅታችን ላይ ለፈፀሙት ቀናነት የጎደለው አሠራር ኃላፊነትን እንዲወስዱና በአስቸኳይ እርምት እንዲደረግ፣ አሠራሩም በመተዳደሪያ ደንባችንና በጋራ የስምምነት ሰነዳችን መሠረት እንዲሆንና ትኩረታችን መጀመሪያውኑ ለመድረኩ መፈጠር አስፈላጊ በሆኑት አገራዊና ሕዝባዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ እንዲሆን በማሳሰብ ጭምር ነው:: ኢዴአን ለመድረኩ ብሔራዊ ተልእኮዎች እውን መሆን ያለውን ቁርጠኝነት በድጋሜ ሲገልፅ ድርጅታዊ መብቱን ሳያስከብር ለዜጎች መብትና ክብር ሊቆም አይቻለውምና መብቱን ለማስጠበቅ ሁኔታው የሚጠይቀውን ከማድረግ ወደ-ኋላ እንደማይልም በግልፅ ማሳወቅ ይፈልጋል::*

*በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል የሚገኙ የመድረኩ አባል ድርጅቶች አባላት ለተሻለ ሥርዓት እውን መሆንና ለመብታቸው መከበር የሚያደርጉት ትንንቅ የድርጅቶችን መፈራቀቅ ሣይሆን የተሻለ መግባባትን፣ መከባበርን፣ መቀራረብንና መተሣሰብን የሚጠይቅ ፈታኝ ጊዜ ነው:: ድርጅታችን የካቲት ሃያ ሁለት ቀን ትግራይ ውስጥ መድረኩን ወክለው በቀጣዩ ምርጫ ለመወዳደር የተዘጋጁት አቶ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ ላይ የተፈፀመው ግድያ በዚያ የሰላም፣ የአንድነትና የፍትኅ ታጋይ ዜጋ ላይ ብቻ ሣይሆን በማንም ሰላም ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፈላጊ ኢትዮጵያዊ ላይ የተፈፀመ ወንጀል አድርጎ ይቆጥረዋል:: በዚኸ አጋጣሚም ለታጋዩ ወንድማችን ቤተሰብ የተሰማንን ሐዘን እንገልፃለን:: የዚኸ ታጋይ ሕይወት በአጭር መቀጠፉ የሚያሣየውና የሚያመላክተው ሰላማዊ ትግሉ ምን ያኸል ፈታኝ እንደሆነና ምርጫው እየተቃረበ ሲሄድም በርካታ ያላስፈላጊና ሁኔታውን የሚያባብሱ፣ አገራችንን ወደባሰ ቀውስ ሊወስዱ የሚችሉ እንቅፋቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ነው:: ታዲያ መድረኩም ሆነ ሌሎች ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች ወደፊት ከምናልባታዊነት ባለፈ መልኩ ሊከሰቱ የሚችሉ የሰላም ትግል እክሎችና ውስብስብ ሁኔታዎችን በማሰብ አንድነታቸውን ማጠንከር ይጠበቅባቸዋል:: የገዥው ፓርቲ አባላትም እንዲሁ ሁኔታውን ከሚያባብስና አገራችንና ሕዝባችንን ወደ አጉል አቅጣጫ ከሚወስድ አድራጎት በመቆጠብ የሁላችንም በሆነች አንዲት አገር ተግባብቶና ተቻችሎ መኖር የሁሉም ጥቅም መሆኑን አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል እንላለን::*

*የማንም መብት በሌላው መብት መነፈግና መረገጥ ላይ ሊጠበቅ አይችልም!*
*መተባበርር በመከባበር!!*

**----------------- // // ------------------**

## ሐተታ፤

## ምርጫ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል፤

በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በተደነገገውና ባለው የምርጫ ሕግ መሠረት በአገራችን አገር-አቀፍ፣ የአካባቢና የወረዳ ምርጫዎች በየወቅቱ ይካሄዳሉ:: በዚኽም መሠረት በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ አጠቃላይ አገር-አቀፍ ምርጫ ይካሄዳል:: ስለሆነም እነሆ በዚኽ ዓመት ምርጫ ሁለት-ሺህ-ሁለት ተደግሷል:: ይኽንን የምርጫ ዑደት ገዢው ፓርቲ በአገራችን ለዴሞክራሲ ሥር መስደድ ዋና ምስክር እንደሆነ በድፍረት ይገልፃል::

እንደሚታወቀው ከአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ በአገራችን ምርጫ ሲካሄድ ቆይቷል:: ደርግም እንዲሁ “የላብ-አደሩን የበላይነት” የሚያረጋግጥ ሥርዓትን ለማስፈን ሕዝብ ወጥቶ “እንዲመርጥ” ያደርግ እንደነበር የትላንት ትዝታ ነው:: ምንም እንኳ ተመሣሣይነትም ልዩነትም እንዳላቸው ቢታወቅም፣ በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘመንም ይሁን በደርግ ጊዜ ከተደረጉ ምርጫዎች በኢሕአዴግ ጊዜ የተደረጉት ምርጫዎች የሚሻሉበት ጎን አላቸው:: ከነዚኽም ዋናው በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከገዢው ክፍል ውጭ አማራጮቻቸውን ለሕዝብ የሚያቀርቡና ከገዢው ጋር የሚፎካከሩ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸው ነው:: ይኽ በሕዝብ ትግል የተገኘ እውነታ እሰየው የሚያሰኝና ሊዳብርና የተሻለ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚገባው በጎ ጎን ነው:: ሆኖም ግን ምርጫን በተመለከተ ሦስቱንም የቅርብ ጊዜ መንግሥታት የሚያመሣሥላቸው ባኅሪ እንዳለ ደግሞ ግልፅ ነው:: በዋናነት የሚያመሣስላቸው የምርጫው ውጤት ዞሮ ዞሮ ገዢውን ክፍል “አቸናፊ” የማድረጉ ሂደት ነው:: ይኽ የሚሆንበትም ምክንያት የምርጫው ዝግጅት፣ ሂደትና አፈፃፀም በገዢው ክፍል ሙሉ ቁጥጥር ሥር ስለሆነ ነው:: ያም በመሆኑ የምርጫው ዓላማና ግብ ገዢው ክፍል ይዞታውን አድሶ የቆመለትን ሥርዓት ለማስቀጠልና በሥልጣን ላይ ተደላድሎ ለመቆየት ብቻ ይሆናል ማለት ነው:: ስለሆነም ነው ብዙዎች የምርጫው ውጤት ተሰልቶ የተቀመጠ ነው ማለት የሚደፍሩት::

ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ አንዳንድ ወገኖች ከምርጫ ዴሞክራሲ እንደሚወለድ (እንደሚፈልቅ) አድርገው በማየት በምርጫ በመሣተፍ ዴሞክራሲን እንገነባለን የሚል የተዛባ አስተሳሰብን ያራምዳሉ:: አንድን መርጫ ትክክለኛ፣ ነፃና ፍትኃዊ የሚያደርገው ሕዝብ በራሱ ነፃ ፍላጎትና እምነት በምርጫው ሂደት ሲሣተፍና ውጤቱም እንደ ሂደቱ የመራጩ ሕዝብ እውነተኛ ፍላጎት የተንፀባረቀበት ሲሆንና አስቀድሞ ያልተወሰነ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው:: በመሠረቱ ማንኛውም ምርጫ ሕዝብ ከቀረቡለት አማራጮች መኻል ለበጎና የተሻለ ተስፋው ይሆነኛል የሚለውን ሰው ወይም ወገን (ፓርቲ) ኃላፊ፣ ተጠሪ ወይም ተወካይ እንዲሆነው በነፃ ፍላጎቱ መርጦ ሥልጣንን ለተወሰነ ጊዜ በአደራዊ እምነት የሚሰጥበት ተግባር ነው::

ምርጫ ሂደት ነው:: ስለሆነም ምርጫ ሲባል ድምፅ በሚሰጥበት ቀን ድምፅን በምርጫ መስጫ ሣጥን ውስጥ የማስቀመጡ ተግባር ብቻ አይደለም:: የምርጫን ውጤት የሚወስነው ድምፅ ከሚሰጥበት ቀን አስቀድሞ ባሉ ዓመታትና በርካታ ወራት መራጩ ሕዝብ ያለ ማንምና ምንም ጣልቃ-ገብነት ወይም ያለ ልዩ ልዩ ግልፅና ስውር ጫናዎች የቀረቡለትን አማራጮች በደንብ ማጥናትና መመዘን የሚያስችል ሁኔታ ሲኖር እንደሆነ ግልፅ ነው:: ይኽ ደግሞ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በመራጩ ሕዝብ መኻል ተገኝተው አማራጫቸውን ማሣወቅና ሕዝብም እንዲያውቃቸውና እንዲመዝናቸው ዕድል ሲኖራቸው ነው:: ታዲያ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ እየሠራ ያለው ሕገ-መንግሥት ይኽን ሁሉ ይፈቅዳል:: እንደ አገራችን ዴሞክራሲ ዳዴ የሚልባቸውና ሰብዓዊ መብቶች በሕግ ከመደንገግ ውጭ በተገቢው መንገድ በተግባር በማይረጋገጡባቸው “ታዳጊ” አገሮች ላይ በስፋት እንደሚታየው በማንኛውም ደረጃ፣ በተለይም ደግሞ በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ምርጫዎች ዋነኛ ዓላማ ገዢው ክፍል (ፓርቲ) አንዴ የያዘውን ሥልጣን እስከ-ወዲያኛው እንዲቀጥል ማድረግ ሆኖ ይገኛል:: ያም በመሆኑ ውጤቱ የሕዝቡን ትክክለኛ ፍላጎት የማያንፀባርቅና ተስፋውን የማያሟላ ይሆናል:: ይኽ ደግሞ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነው ሕዝብ በሚደረጉ ምርጫዎች የሚሣተፈው በሙሉ ልቦናው የሚፈልገውን ለውጥ ያስገኝልኛል ብሎ በማመንና መሠረታዊ መብቱ ስለሆነ ሣይሆን መሣተፍና አልፎም ለገዢው ክፍል መምረጥ በልዩ ልዩ ጫናዎችና

ምክንያቶች እንደ ግዴታ ስለሚሆንበት ነው።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴአን) በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የምርጫ ሁለት-ሺህ-ሁለት ሂደት የሚመለከተው በሂደትነቱ ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ምርጫ ሂደት ስለሆነ ድርጅታችን ምርጫ ሁለት-ሺህ-ሁለትን የሚያየው እንዳለፉት ምርጫዎች ሁሉ የአንድ ሰሞን ግርግርና መጥቶ የሚያልፍ የአንድ ጊዜ ክስተት አድርጎ ሣይሆን የሥልጣን ምንጭ የሆነው ሕዝባችን የሥልጣኑ ሙሉ ባለቤት እንዲሆን ለሚያበቃው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በሚደረገው ቀጣይ ሰላማዊ ትግል ማእከልነቱን መልሶ እንዲጨብጥ ከሚኖረው አዎንታዊ አስተዋፅዖና ጠቀሜታ አኳያ ነው። ድርጅታችን ሕዝብን የሥልጣኑ ባለቤት የሚያደርግ የፍትኅና የእኩልነት ሥርዓት ከምርጫ እንደማይወለድ ጠንቅቆ ያውቃል። የዴሞክራሲ እሴቶች በሌሉበት ሁኔታ ምርጫ ዴሞክራሲን አያስገኝም። ዓለም-አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ፣ የሕዝብን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ፣ መብቶቹን የሚያረጋግጥ፣ ታማኝና ተቀባይነት ያለው ውጤት የሚኖረው ምርጫ እውን እንዲሆን በነፃ የመናገር፣ የመደራጀት፣ የመሣሰሉት ቅድመ-ሁኔታ መብቶች የተባሉትና የዴሞክራሲ ተቋማት መኖርና መረጋገጥ ዴሞክራሲን እውን የሚያደርግ ምርጫ እንዲኖር ያስችላል።

በነፃና ርቱዓዊ ምርጫ በምርጫ መሣተፍ አለመሣተፍ፣ ድምፅ መስጠት አለመስጠት፣ ውጤቱ የተሰጠውን ድምፅ በትክክል የማያንፀባርቅ ሆኖ ሲገኝ ውጤቱን መቀበልም ይሁን አለመቀበል ሁሉ ማንኛውም ነፃ ዜጋ ያለ ስጋትና መሳቀቅ በተግባር ሊለማመድባቸውና ሊፈጽማቸው የሚገቡ መሠረታዊ መብቶች ናቸው። በቅርቡ በገዥው ፓርቲና በተወሰኑ ድርጅቶች መኻል የተፈረመው “የሥነ-ምግባር” መመሪያ ችግር ሆኖ ያየነው ከፈረሱ በፊት ጋሪው ዓይነት አካሄድ ስለሆነ ነው። የጨዋታ መስኩ ሳይስተካከልና አንዱ ወገን ሕጉን አስፈፃሚም፣ ዳኛም ተወዳዳሪም በሆነበት ሁኔታ ከጫማ ላይ የእግር ሹራብ የማድረግ ዓይነት የግርንቢጥ አካሄድ ስለሆነ እንኳን የሕዝባችንን የተፈራረሙትን ድርጅቶችና አባላቱን ጥቅም በትክክል አያስጠብቅም፣ አያስተባቃም የሚል ስጋት አለን። በኛ እምነት ይኸ “ውል” ተቃዋሚው ክፍል ልዩነቱን አቻችሎና አዋውጦ አንድ ላይ በመቆም ከገዥው ፓርቲ ጋር የአገርንና የሕዝብን ጥቅም ባስቀደመና እንደ አንዲት አገር ዜጎች በእኩልነት መንፈስ ሕዝብ እያወቀውና በግልፅ ከሚደረግ ምርጫውን ነፃና ፍትኃዊ ለሚያደርግ የሰከነ ድርድር ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ የሚመጣ እንጂ ከወዲሁ ምንም ምን ሳይያዝ ውጤቱ በውዴታ የነገ እንቅፋትና መሰናክሎችን አስቀድሞ ለሚዘረጋና ውሎ አድሮ በራስ ላይ “እኔን ያየህ ተቀጣ” ዓይነት የአደጋና የፀፀት ምልክትን ተሸክሞ አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ከመሆን ሊያልፍ ከማይችል ትእይንት ውስጥ የሚያስገባ ጉዳይ መሆን አልነበረበትም።

ኢዴአን በዚኽ ምርጫ ሂደት የሚሣተፈው ከፍ ሲል በጠቀስነው እልህ-አስጨራሽ የሆነውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትግል በሚያግዝ መልኩ እንዲካሄድ በማሰብና ከዚያም አኳያ በማየት ነው። ስለሆነም የድርጅታችን ትኩረት የምርጫ ቀን በሚገኘው ውጤት ላይ በቁንፅል የተንጠለጠለ ሣይሆን ሕዝባችን በዚኽና ከዚኽ ሂደት የበለጠ የሚደራጅበትና አንድነቱን የተሻለ የሚጠናከርበት ሂደት እንዲሆን ነው። ገዥው ፓርቲ ይሁን ሌሎች ወገኖች በአገራችን ምርጫ በየወቅቱ መደረጉን ዴሞክራሲ እንደሰፈነ አድርገው ቢያቀርቡም፣ እነሱ ምርጫ ሲሉ እኛ ዴሞክራሲ ስንል መሠረታዊ የአመለካከትና የእምነት ልዩነቱ የት ላይ እንደሆነ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል። በኛ በኩል አሁንም እውነተኛና ፍትኃዊ ምርጫ ከዴሞክራሲ ይፈልቃል እንጂ ዴሞክራሲ ከምርጫ ከቶውን ሊገኝ እንደማይችል እያስገነዘብን፤ ይልቅስ በዚኽ ሁኔታ ከሚገኝ ጊዚያዊ ሥልጣን ይበልጥ ከዚኽ ምርጫ ማዶ በማየት ሁሉም ተጠቃሚና አትራፊ ለሚሆንበትና አገራችን ለወደፊት ትውልዶች የተሻለች አገር እንድትሆን ለሚያደርግ የእኩልነትና የፍትኅ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑት ዴሞክራሲያዊ እሴቶች እውን እንዲሆኑ ሁላችንም፣ በተለይ ገዥው ፓርቲ ታሪካዊ ድርሻችንን እንድንወጣ አደራ እንላለን።

ምርጫችን እንደትግላችን ከዴሞክራሲ ለሚወለድ ፍትኃዊ ምርጫ ይሁን!
የተባበረ የሕዝብ ትግል ምን-ጊዜም አቸናፊ ነው!!